የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ
The Holy synod of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church

No 2038/2011
Date 1.1.2007

አንተሰ አንተ ክመ ወዓመቲከኒ ዘኢየኃልቅ
አንተ ግን ያው አንተ ነህ ፥
ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም ፡፡
መዝ 101 ፥ 27 ፡፡

ዘመናትን አሳልፎ የሚኖር ከዘመናት በፊትም የነበረ የቅዱሳን አባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ በሰላም አሸጋገራችሁ!

አዲሱ ዘመን የሰላም የጤና እንዲሆንላችሁ የዘወትር ጸሎትና ምኞታችን ነው ፡፡

በአገር ውስጥና በመላው ዓለም ለምትገኙ ኢትዮጵያን ወገኖቻችን ! ከሁሉ አስቀድሞ እግዚአብሔር በቸርነቱ ጠብቆ ይህን አዲስ ዘመን ከሰጠን ፥ በተሰጠን አድል የመጠቀም ሰብአዊ ግዴታ እንዳለብን ማሳሰብ እንወዳለን ፡፡ እሁን ባለንበት ዘመን በዓለማችን የሚታየው የሰው ልጆች ችግር ከአቅም በላይ እየሆነ መጥቷል ፡፡ የመንግሥታት በሃይማኖት ጣልቃ ገብነት የሚፈጥረው የሃይማኖት ልዩነት ችግር ፣ መንግሥታት የፖለቲካ ችግራቸውን በውይይት መፍታት ሲችሉ ፥ ኃይልን መሠረት ያደረገ የችግር መፍቻ ስልት ስለሚጠቀሙ ፥ የጎሣ ግጭቶች በዝተዋል ፡፡

በዚህም ምክንያት የዓለም ኢኮኖሚ አንድ አቅጣጫ ይዞ መሄድ እቅቶታል ፡፡ እንደዚሁም በዓለም ላይ አብላጫው ሕዝብ በረኀብ አለንጋ እየተገረፈ ይገኛል ፡፡ በተለይም በኢትዮጵያውያን ላይ እየተደረገ ያለው የግፍ ጽዋ ሞልቶ እየፈሰሰ ነው ፡፡ ከመጠንም አልፎ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እየተቸገረበት ነው ፡፡ ኢትዮጵያውያን በዓለም አቀፍ አየር ማረፊያዎች እንኳ በነጻነት መንቀሳቀስ አልቻሉም ፡፡ የበረራ ሰዓታቸውን ሲጠብቁ በባዕድ የጸጥታ ሠራተኞች ተገድደው ለሚቃወማቸው መንግሥት የሚሰጡ ከሆነ ፥ በመላው ዐለም ለተበተነው ኢትዮጵያዊ ወገናችን ምን ዋስትና ይኖረዋል? ፡፡

ይህን ሁሉ ዘወር ብለን በመመልከት አዲሱን ዘመን ፥ አዲስ መፍትሔ የምንፈለግበት ዘመን ልናደርገው ይገባል ፡፡ ውድ ወገኖቻችን ! አሁን ስለ ሌሎች የምናወራበት ጊዜ አይደለም፡፡ ይልቁንም እያንዳንዳችን ለወገኖቻችን ምን እናድርግ ? ለሰላምና ለይቅርታ ምን አደረግሁ ? ብለን መጠየቅ አለብን ፡፡ የራስን ሐሳብ ብቻ በማዳመጥ ግማሽ ምእት ዓመት በከንቱ አለፈ ፡፡ ስለዚህ ምን ማድረግ አለብን? ብሎ መጠየቅ ታላቅ ብልህነት ነው፡፡

ብዙዎቻችን በልዩነቶቻችን ምክንያት በጥላቻ ስሜት ውስጥ ነን ፡፡ ለዚህ የይቅርታ ልብ ያስፈልገናል ፡፡ የቀድሞ አባቶቻችን በይቅር ለእግዚአብሔር ላይ በተመሠረተ ይቅርባይነት ብዙ ለውጥ ያመጡ ነበር ፡፡ "በቀል የኔ ነው" ያለውን አምላካዊ ቃል መሠረት አድርገው ፥ ጥላቻን ሳይውል ሳያድር ከመካከላቸው እያስወገዱ አንድነታቸውን ጠብቀው ኖረዋል ፡፡

4127 Redwood Rd. Oakland CA 94619 Tel: (510) 530 3681

የአሁኑ ትውልድ የአገሩን አንድነት ብቻ ሳይሆን የእነሱን የይቅርታ ጥበብ ጭምር መረከብና በሥራ ላይ ማዋል ይገባዋል ። ይህ ጉዳይ ፥ በፖለቲካ ልዩነት ላይ ያሉትን ወገኖችንም ይመለከታል ።

ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ተቻችሎ ለመኖር አስተማሪ አይፈልጉም ። የሃይማኖት አክራሪነት ካለ የአሁኑ መንግሥት ፖለቲካ የፈጠረው ነው ። ፖለቲከኞች ቀድሞም ቢሆን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ሃይማኖቶችን ይጠቀሙ ነበር ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በራሱ ተነሣስቶ አንዱ በሌላው እምነት ላይ የፈጸመው በደል እንደሌለ እርግጥ ነው ። ስለዚህ በአሁኑ ወቅት እንደ ልዩ መቀስቀሻ ሆኖ እየቀረበ ያለው የእምነት ጽንፈኝነት ፥ ከሃይማኖቱ ተከታዮች ሊሆን አይችልም ። ለዚህ መሣሪያ መሆን የሚፈልጉ ካሉ ወደ ልባቸው ተመልሰው ራሳቸውን እንዲመለከቱ እናሳስባቸዋለን ። የዚህ ዐይነት ጉዞ ጥላቻን ከማትረፍ በስተቀር ፥ እስካሁን እንዳልሠራ ሁሉ ፥ አሁንም ወደፊትም አይሠራም ።

በዓለም ዙሪያና በሀገር ውስጥ የምትኖሩ ወገኖቻችን ! ዛሬ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከሞት አፋፍ ላይ ናት ። ሁሉም ሰው በዚህ እውነታ ይስማማል ። ሁኖም ግን ስምምነት ላይ ያልተደረሰው እንዴት እናስቁመው ከሚለው ላይ ብቻ ነው ። ቤተ ክርስቲያን የዚህ መፍትሔ ሩቅ ነው ብላ አታምንም ። ችግሩን ያረዘመው መፍትሔ ጠፍቶ አንዳልሆነ እናምናለን ። የችግሩ መፈትሔ ማጣት ለመፈትሔው መሥራትና አለመሥራት ነው ። መፍትሔውም በተቃዋሚው ጎራ በኩል አንድነት መፍጠር ብቻ ነው ። የሀገራችንን ሁኔታ ውስብስብ ያደረገው ፥ ገገርው መንግሥት ብቻ ሳይሆን ፥ የተቃዋሚው አንድ አለመሆን ጭምር ነው ። ስለዚህ በዚህ አዲስ ዓመት ፥ በአዲስ ልብና በአዲስ ሐሳብ ተነሣሥተን ሀገራችንን ከጥፋት ሕዝባችንን ከመከራ እንድናተርፍ በቤተክርስቲያን ፣ በሀገራችንና በሕዝባችን ስም ጥሪ እናቀርባለን።

ልዑል እግዚአብሔር ዘመኑን ይባርክልን

ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ